# አምልኮተ እግዚአብሔር

**በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ አሜን።**

## ስግደት

ክርስትና በአንደበት ብቻ አይኖርም። በመምሰል አይገፋም። ማኅተብ በማሰር ብቻ አይገለጽም። ብዙ በማገልገል ብቻ አይጸናም። በጾም ጸሎት ብቻ አይገደብም። ቤተክርስቲያን በመሳለም ብቻ አይወሰንም። አድባራት በመጎብኘት ብቻ አይገደብም። የክርስትና መሠረት ይህ ቅዱስ ቃለ-ትእዛዝ ነው።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 22)

37፤ ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።

38፤ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።

ታላቂቱና የቀደመቺው ትእዛዝ ይህቺ ናት። ፍጥረታት ሁሉ ከዚህች ትእዛዝ ይነሣሉ። የሰው ልጆች የመጀመሪያ ትልቂቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህም፥ በፍጹም አሳብህም ውደድ።

መውደድን ከምን አስነሥቶ ጠቀመ? ከልብ ነው የጀመረው። መውደድ ከልብ ይጀምራል። ዘወትር በሄድንበትና በቆምንበት ሁሉ፣ በሆነልንና በማይሆንልንም ልክ፣ ከውስጣችን አምላክን ማፍቀር ከልብ መውደድ ነው። ይህ የልብ መውደድ ወደ ነፍስ ይሄዳል። በዚህ ጊዜ 'እኔ' እንተውና 'እርሱ' እንላለን። 'ከእርሱም ለእርሱ' እንላለን። እስከ ጥልቅም መሥዋትነት እናፈቅረዋለን። በመጨረሻው በፍጹም አሳብህ ይላል። አሳብ ታዲያ በሕሊናችን ጓዳ ተጸንሶ ወደ ውጪ የሚወለድ ግልጽ ውጤት እንጂ ተጨንግፎ የሚቀር ብቻ መሆን አይገባውም። መገለጥ ይገባዋል። መታየት ይገባዋል። መተግበር ይገባዋል።

እነሆም ከልባችን አስጀምረን፤ በነፍሳችን አኑረን፤ በአሳባችን የምንይዘው ፍቅር የሚታየው በምግባራችን ብቻና ብቻ ነው። የሚጨበጠው ሲተገበር ነው። የሚኖረውም ሲተገበር ነው።

ስግደት አንዱ ታላቅ የፍቅራችን መግለጫ፣ የመገዛታችን መታያ፣ የአክብሮታችን ውጤት፣ የተፈጥሮአችን ዓላማ፣ የጸጋችን መነሻ፣ የሞገሳችን ምንጭ፣ የኃይላችን መገኛ፣ ዲያቢሎስን ማሸነፊያ፣ በጠቅላላው እንደ እስትንፋስ መኖሪያ ነው።

እናስተውል!!!

ዲያቢሎስና የሰው ልጆች የምንለይበት ትልቁ ድንበር ስግደት ነው። ክፉ ኃይላት ከሰማይ የተባረሩት አንገዛም ብለው ነው። አንሰግድም ብለው ነው። አንወድቅም ብለው ነው።

ታዲያም የሰው ልጅ በወደቀው የጨለማው ሠራዊት ምትክ ክብሩን ለመውረስና ምሥጋናውን ለማድረስ ሲፈጠር ይህንን ተከትሎ ነው። በትዕቢት አንወድቅም ባሉት ሠራዊት ፋንታ በፍቅር እንወድቃለን የሚሉን፣ አንገዛም ባሉት ሠራዊት ፋንታ እንገዛለን የሚሉን፣ አንሰግድም ባሉት እብሪተኞች ምትክ የሚሰግዱ ነገዶች ናቸው የሰው ልጆች። ከዚህ ውጪ የሆነ ሰው ካለ፤ በማወቅም ባለማወቅም ከዲያቢሎስ ሕልውናና ጠባይ ጋራ አንድ ሆኗል ማለት ነው።

ስግደት መለኮታዊ ኃይል ማምጫ ነው። ስግደት ክፉውን መቁረጫ ነው። ስግደት የጸጋ ማሳደጊያ ነው። ስግደት የመንፈሳዊ ሥልጣን መበልጸጊያ ነው። ስግደት የጸሎት ማጽደቂያ ነው። ስግደት የተግባር ሃይማኖት መግለጫ ነው። ስግደት የእምነት

ጉልበት መጨመሪያ ነው። ስግደት ሰውነትን ለፍቅር ማስገዢያ መንገድ ነው። በመሆኑም ስግደት ለክርስቲያን የሕይወቱ ክፍል ሊሆን ይገባል።

© ከመምህር ግርማ ተማሪ ናትናኤል ሰለሞን

የአምልኮት ስግደት በጭራሽ ሰግዳችሁ ለማታውቁ ሰዎች ከዚህ 28ቱ ስግደት ተነሡ። ቢያንስ ቢያንስ በቀን ሁለቴ መስገድ ጀምሩ። ዛሬ ጀምሩ። እሳት ካልተነካ ማቃጠሉ እንደማይታወቅ፣ ስኳር ካልተቀመሰ መጣፈጡን እንደማንረዳው፤ ስግደቱንም መስገድ ካልጀመራችሁ የሚሰጠው የውስጥ ኃይል፣ ሰላም፣ እፎይታ፣ መረጋጋትና ማስተዋል መጀመር መቼም አይገባችሁም።

## መነሻ የአምልኮት ስግደት

በ ማ ለ ዳ ን ቁ

የአምልኮት ስግደት

ለአብ እሰግዳለሁ

ለወልድ እሰግዳለሁ

ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ

ምስጋና ይሁን ለአብ

ምስጋና ይሁን ለወልድ

ምስጋና ይሁን ለመንፈስ ቅዱስ

ሃሌሉያ ለአብ

ሃሌሉያ ለወልድ

ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ

በረከቱን ለሰጠን

ኃይሉን ላበዛልን

በዚህ ሰዓት ላቆመን

በቸርነቱ መንገድ ለመራን

በዚህ ሰዓት በጸጋው ለጠበቀን

ንቁ

በብርሃኑ መንገድ ለመራን

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

የድንግል ማርያም ልጅ

ክብር ምስጋና ይግባው

ለዘለዓለሙ አሜን።

ከጀማሪ አለፍ ላላችሁ፥ መስገድ መንበርከክ የጀመራችሁ ከበታች ያለውን የአምልኮት ስግደት ከ7ቱ ጸሎተ ሰዓታት ውስጥ ችላችሁ ጸሎት በገባችሁበት ሰዓት ሁሉ ስገዱ። ቢያንስ ቢያንስ ግን በቀን ሁለቴ ጠዋትና ማታ ስገዱ።

## 41 የአምልኮት ስግደት

እሰግድ ለአብ

እሰግድ ለወልድ

እሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ

እሰግድ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ (3X)

በ
ማ
ለ
ዳ
ን
ቁ

ስብሐት ለአብ

ስብሐት ለወልድ

ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ምስጋና ለአብ

ምስጋና ለወልድ

ምስጋና ለመንፈስ ቅዱስ

ሃሌሉያ ለአብ

ሃሌሉያ ለወልድ

ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ

ንቁ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ (3X)

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ እብኖዲ

ቅዱስ ታዖስ

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

የአምልኮት ስግደት

እስከዚች ግዜ ላደረሠን ፣

በመለኮቱ ኃይል ለጠበቀን ፣

ፍፁም ፍቅሩን ለሰጠን ፣

ቸርነቱን ላበዛልን ፣

በብርሃኑ መንገድ ለመራን ፣

ኃጢአታችንን ለታገሠልን ፣

በሥጋወ ደሙን ለባረከን ፣

ለድንግል ማርያም ልጅ

ለልዑል እግዚአብሔር

አምልኮም ምስጋናም ክብርም ይግባው

ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን

## መናፍስትን የሚቀጠቅጥ የአምልኮት ስግደት

እሰግድ ለአብ

እሰግድ ለወልድ

እሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ

እሰግድ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ቅዱስ እግዚአብሔር ኃይል ሁነኝ

ቅዱስ ኃያል ሥልጣን ሁነኝ

ቅዱስ ሕያው ብርታት ሁነኝ

ቅዱስ አዶናይ ጉልበት ሆነኝ

ቅዱስ ኤልሻዳይ ግርማ ሁነኝ

ቅዱስ ያሕዌ ጽናት ሁነኝ

ቅዱስ ጸባዖት ምርኩዝ ሁነኝ

ቅዱስ ማስያስ በረከት ሁነኝ

ቅዱስ ትስቡጣ ጸጋና ሞገስ ሁነኝ

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል አሜን።

በማለዳ ንቁ

ለሚያስደነግጥ መለኮታዊ መብረቅ እሰግዳለሁ

ለተንቦገቦገ መለኮታዊ ፍሕም እሰግዳለሁ

ለተወርዋሪ መለኮታዊ ቀስት እሰግዳለሁ

ለሚያቃጥል መለኮታዊ እሳት እሰግዳለሁ

ለሚያበራ መለኮታዊ ፋና እሰግዳለሁ

ለአንጸባራቂ መለኮታዊ ፀሐይ እሰግዳለሁ

ክቡድ ለሆነ ዕብነ መለኮት እሰግዳለሁ

ንቁ

ለሚያንቀጠቅጥ መለኮታዊ ግርማ እሰግዳለሁ

ለሚንቦገቦግ መለኮታዊ ነበልባል እሰግዳለሁ

ላማረ መለኮታዊ ጋሻ እሰግዳለሁ

ለስኩረ ኃይል መለኮታዊ ጦር እሰግዳለሁ

ለሚያቃጥል መለኮታዊ ግለት እሰግዳለሁ

ለአሸናፊ መለኮታዊ እዘዝ እሰግዳለሁ

ለረቀቀ መለኮታዊ ሥልጣን እሰግዳለሁ

ለብርሃናዊ መለኮታዊ ጸዳል እሰግዳለሁ

የአምልኮት ስግደት

ለተሳለ መለኮታዊ ሰይፍ እሰግዳለሁ

ለሚያስፈራ መለኮታዊ ቃል እሰግዳለሁ

ለአስደናቂ መለኮታዊ ነበልባል እሰግዳለሁ

ለሚቀራርጥ መለኮታዊ ገጀሞ እሰግዳለሁ

ለንጹሕ መለኮታዊ ባሕርይ እሰግዳለሁ

ለጽኑ መለኮታዊ ምሣር እሰግዳለሁ

ለምጡቅ መለኮታዊ ተራራ እሰግዳለሁ

ለተነጣጠረ መለኮታዊ ቀስት እሰግዳለሁ

ለትኩስ መለኮታዊ ሙቀት እሰግዳለሁ

ነበልባሉን ላስረዘመ መለኮታዊ እሳት እሰግዳለሁ

ለአሸናፊ መለኮታዊ ኃይል እሰግዳለሁ

ገዥነት ላለው መለኮታዊ ገናንነት እሰግዳለሁ

የአድማስ ሰፋት ላለው መለኮታዊ ብርሃን እሰግዳለሁ

በእሳት ለተከበበ መለኮታዊ ዙፋን እሰግዳለሁ

እውነት በእውነት ለዘላለሙ አሜን።

ለበረታችሁ፤ የስግደት አቅማችሁን ማሳደግ ለምትፈልጉ፤ ክፉ መናፍስትን የማዳከም ውጊያን ጉልበት ለመስጠት ለምትሹ፤ ከዚህ በታች ያሉትን ረዘም ያሉ ስግደቶችን መስገድ ነው።

## የአምልኮት ስግደት

በማለዳ ንቁ

ሥላሴ ሆይ ወደኔ ና 3X
እግዚአብሔር ሆይ ወደኔ ና 3X
አምላክ ሆይ ወደኔ ና 3X

እሰግዳለሁ ለአብ 3X
እሰግዳለሁ ለወልድ 3X
እሰግዳለሁ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ፍቅር ነህ አዎ ፍቅር ነህ 3X
ቅዱስ ነህ አዎ ቅዱስ ነህ 3X
ብርሃን ነህ አዎ ብርሃን ነህ 3X
ኃያል ነህ አዎ ኃያል ነህ 3X
መሐሪ ነህ አዎ መሐሪ ነህ 3X
ንጉሥ ነህ አዎ ንጉሥ ነህ 3X
ከሃሊ ነህ አዎ ከሃሊ ነህ 3X
ሐሊብ ነህ አዎ ሐሊብ ነህ 3X
የማለዳ ጎሕ ነህ አዎ የማለዳ ጎሕ ነህ 3X
እረኛችን ነህ አዎ እረኛችን ነህ 3X
የወይን ግንድ ነህ አዎ የወይን ግንድ ነህ 3X
የሕይወት ውኃ ነህ አዎ የሕይወት ውኃ ነህ 3X
ሰማያዊ እንጀራ ነህ አዎ ሰማያዊ እንጀራ ነህ 3X
የእውነት መንገድ ነህ አዎ የእውነት መንገድ ነህ 3X

ንቁ

የመለኮት እሳት ነህ አንተ እሳት ነህ 3X
የመለኮት ጋሻ ነህ አንተ ጋሻ ነህ 3X
የመለኮት ፀሐይ ነህ አንተ ፀሐይ ነህ 3X
የመለኮት ሰይፍ ነህ አንተ ሰይፍ ነህ 3X
የመለኮት ፋና ነህ አንተ ፋና ነህ 3X
የመለኮት ነበልባል ነህ አንተ ነበልባል ነህ 3X

ምስጋና ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X
ሃሌሉያ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X
ስብሐት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

የአምልኮት ስግደት

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አዶናይ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ኤልሻዳይ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ያሕዌ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ጸባኦት
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ኢየሱስ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ክርስቶስ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ መድሃኒተ ዓለም

በአምሳሉ ለፈጠረን
ፍጹም ኃይሉን ለሰጠን
በዚህ ጊዜ ለጠበቀን
ምሕረቱን ላበዛልን
ኃጥኢታችንን ለተወልን
በክቡር ደሙ በቅዱስ ሥጋው ላነገሠን
አባት ለሆነን ኃያል አምላክ
ፍጹም ክብርና ፍጹም አምልኮት ይግባው
ዛሬም ዘወትርም አሜን።

# የአምልኮት ስግደት

ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ወደኔ ና 3X
አማኑኤል ሆይ ወደኔ ና 3X
መድኃኒተዓለም ሆይ ወደኔ ና 3X

ለአብ እሰግዳለሁ 3X
ለወልድ እሰግዳለሁ 3X
ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ 3X

አብ ቅዱስ ነው 3X
ወልድ ቅዱስ ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ  ቅዱስ ነው 3X

አብ ፀሐይ ነው 3X
ወልድ ፀሐይ ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ ነው 3X

አብ ፍቅር ነው 3X
ወልድ ፍቅር ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ ፍቅር ነው 3X

አብ እሳት ነው 3X
ወልድ እሳት ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ እሳት ነው 3X

አብ ብርሃን ነው 3X
ወልድ ብርሃን ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ ብርሃን ነው 3X

አብ ጉንድ ወይን ነው 3X
ወልድ ጉንድ ወይን ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ ጉንድ ወይን ነው 3X

አብ መለኮታዊ ቀስት ነው 3X
ወልድ መለኮታዊ ቀስት ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ቀስት ነው 3X

አብ መለኮታዊ ብርሃን ነው 3X
ወልድ መለኮታዊ ብርሃን ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ብርሃን ነው 3X

በማለዳ ንቁ

ንቁ

አብ የሃይማኖት መሠረት ነው 3X
ወልድ የሃይማኖት መሠረት ነው 3X
መንፈስ ቅዱስ የሃይማኖት መሠረት ነው 3X

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይልካል 3X
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስለጥናል 3X
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ምስክር ይሆናል 3X

አንዱ አብ ቅዱስ ነው 3X
አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው 3X
አንዱ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው 3X

ምስጋና ይሁን ለአብ 3X
ምስጋና ይሁን ለወልድ 3X
ምስጋና ይሁን ለመንፈስ ቅዱስ 3X

በረከቱን ለሰጠን ፣
ኃይሉን ላበዛልን ፣
በዚህ ሰዓት ላቆመን ፣
በቸርነቱ መንገድ ለመራን ፣
በዚህ ሰዓት በጸጋ ለጠበቀን ፣
በብርሃኑ ኃይል ለመራን ፣
ክብር ምስጋና ይግባው ፣

የአምልኮት ስግደት

ሃሌሉያ ለአብ 3X
ሃሌሉያ ለወልድ 3X
ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ቅዱስ እግዚአብሔር
ቅዱስ ኃያል
ቅዱስ ሕያው
ቅዱስ ኤልሻዳይ
ቅዱስ አዶናይ
ቅዱስ ያሕዌ
ቅዱስ ጸባኦት
ቅዱስ ኢየሱስ
ቅዱስ ክርስቶስ
ቅዱስ አማኑኤል
የድንግል ማርያም ልጅ
አምልኮና ክብር ምስጋና ይግባው።

# የአምልኮት ስግደት

አብ ሆይ ወደኔ ና 3X

ወልድ ሆይ ወደኔ ና 3X

መንፈስ ቅዱስ ሆይ ወደኔ ና 3X

እሰግድ ለአብ 3X

እሰግድ ለወልድ 3X

እሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

በማለዳ ንቁ

አብ ጥበብ ነው 3X

ወልድ ጥበብ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ጥበብ ነው 3X

አብ ፍፁም እውነት ነው 3X

ወልድ ፍፁም እውነት ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ፍፁም እውነት ነው 3X

አብ ኃሕ ነው 3X

ወልድ ኃሕ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ኃሕ 3X

አብ የጽድቅ አክሊል ነው 3X

ወልድ የጽደቅ አክሊል ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የጽድቅ አክሊል ነው 3X

አብ የሃይማኖት ጋሻ ነው 3X

ወልድ የሃይማኖት ጋሻ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የሃይማኖት ጋሻ ነው 3X

ንቁ

አብ ሐሊብ ነው 3X

ወልድ ሐሊብ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ሐሊብ ነው 3X

አብ ዘላለማዊ ነው 3X

ወልድ ዘላለማዊ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው 3X

አብ መለኮታዊ እሳት ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ እሳት ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ እሳት ነው 3X

አብ መለኮታዊ ጦር ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ ጦር ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ጦር ነው 3X

አብ መለኮታዊ ፋና ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ ፋና ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ፋና ነው 3X

ለአብ ምስጋና ይገባል 3X

ለወልድም ምስጋና ይገባል 3X

ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል 3X

ስብሐት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ሃሌሉያ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይወደሳሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያነጻሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያፀራሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያጸናሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስጨክናሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይጋርዳሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያለብሳሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሰውን ይሰባሉ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ባለሟል ያደርጋሉ

እግዚአብሔር አብ ቅዱስ ነው 3X

እግዚአብሔር ወልድ ቅዱስ ነው 3X

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው 3X

ሥሉስ ቅዱስ 3X

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

የአምልኮት ስግደት

ይህንን ኀብስት ላበላን ፣

ይህንንም ጽዋ ላጠጣን ፣

ምግባችንንና ልብሳችንንም ላዘጋጀልን ፣

ከጠላት ወጥመድ ለጠበቀን ፣

ለቅዱሳን አምላክ ለእግዚአብሔር

ውዳሴና መገዛት ይሁን አሜን።

# የአምልኮት ስግደት

ጌታ አዶናይ ሆይ ወደኔ ና 3X

ጌታ አልሻዳይ ሆይ ወደኔ ና 3X

ጌታ ጸባኦት ሆይ ወደኔ ና 3X

እሰግድ ለአሐዱ አብ 3X

እሰግድ ለአሐዱ ወልድ 3X

እሰግድ ለአሐዱ መንፈስ ቅዱስ 3X

በማለዳ ንቁ

አብ መለኮታዊ ፀሐይ ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ ፀሐይ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ፀሐይ ነው 3X

አብ መለኮታዊ መብረቅ ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ መብረቅ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ መብረቅ ነው 3X

አብ መለኮታዊ ሰይፍ ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ ሰይፍ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ሰይፍ ነው 3X

አብ የብርሃን ጸዳል ነው 3X

ወልድ የብርሃን ጸዳል ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የብርሃን ጸዳል ነው.3X

ንቁ

አብ ንጉሥ ነው 3X

ወልድ ንጉሥ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ንጉሥ ነው 3X

አብ የኃይል መንፈስ ነው 3X

ወልድ የኃይል መንፈስ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የኃይል መንፈስ ነው 3X

አብ ከሃሊ ነው 3X

ወልድ ከሃሊ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ከሃሊ ነው 3X

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይመረምራሉ 3X

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይፈርዳሉ 3X

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይጠብቃሉ 3X

በአብ እታመናለሁ 3X

በወልድ እጠበቃለሁ 3X

በመንፈስ ቅዱስ እጸናለሁ 3X

ንጹሕ ምስጋና ለአብ 3X

ንጹሕ ምስጋና ለወልድ 3X

ንጹሕ ምስጋና ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ንስብሖ ለአብ 3X

ንስብሖ ለወልድ 3X

ንስብሖ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ኪያከ ንዌድስ እግዚኦ 3X

ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ 3X

ኪያከ ሃሌሉያ እግዚኦ 3X

ስብሐት ለእግዚአብሔር አብ 3X

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወልድ 3X

ስብሐት ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ 3X

እግዚአብሔር እብኖዲ

እግዚአብሔር ኢያኤል

እግዚአብሔር ማስያስ

እግዚአብሔር ታዳኤል

እግዚአብሔር ትስቡጣ

እግዚአብሔር ታየስ

የአምልኮት ስግደት

ምሕረቱን ላበዛልን ፤

በዚህ ቦታ ላቆመን ፤

ሰላምና ጸጋውን ላካፈለን ፤

ከክፉ መናፍስት ለጋረደን ፤

ሞገሱን ላለበሰን ፤

መከራን ተቀብሎ ነፍሱን ለሠዋልን ፤

ለሠራዊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፤

ክብርና ምስጋና አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን አሜን።

# የአምልኮት ስግደት

ጸባኦት ሆይ ወደኔ ና 3X

እብኖዲ ሆይ ወደኔ ና 3X

ማስያስ ሆይ ወደኔ ና 3X

ለአብ እሰግዳለሁ 3X

ለወልድም እሰግዳለሁ 3X

ለመንፈስ ቅዱስም እሰግዳለሁ 3X

በ ማ ለ ዳ ን ቁ

አብ የብርሃን አዕማድ ነው 3X

ወልድ የብርሃን አዕማድ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የብርሃን አዕማድ ነው 3X

አንድ እግዚአብሔር ጽኑ ፍሕም ነው 3X

አብ የመባርቅት ብልጭታ ነው 3X

ወልድ የመባርቅት ብልጭታ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የመባርቅት ብልጭታ ነው 3X

አንድ እግዚአብሔር ባለ ግርማ ነው 3X

አብ የእሳት ባሕሪይ ነው 3X

ወልድ የእሳት ባሕሪይ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የእሳት ባሕሪይ ነው 3X

አንድ እግዚአብሔር የመለኮት ነበልባል ነው 3X

ንቁ

አብ እውነተኛ ፀሐይ ነው 3X

ወልድ እውነተኛ ፀሐይ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ፀሐይ ነው 3X

አንድ እግዚአብሔር የዓለም ብርሃን ነው 3X

አብ የመለኮት ጦር ነው 3X

ወልድ የመለኮት ጦር ነው 3X

መንፈስ ቅዱስም የመለኮት ጦር ነው 3X

አንድ እግዚአብሔር የእምነት ጋሻ ነው 3X

አብ ሰማያዊ መርከብ ነው 3X

ወልድ ሰማያዊ መርከብ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ሰማያዊ መርከብ ነው 3X

አንድ እግዚአብሔር የጽድቅ መልሕቅ ነው 3X

አብ የትሩፋት አበጋዝ ነው 3X

ወልድ የትሩፋት አበጋዝ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የትሩፋት አበጋዝ ነው 3X

አንድ እግዚአብሔር የባሕሪይ ባለጸጋ ነው 3X

ምስጋና ይገባል ለአብ 3X

ምስጋና ይገባል ለወልድ 3X

ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ሃሌሉያ ለአብ 3X

ሃሌሉያ ለወልድ 3X

ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ስብሐት ለአብ 3X

ስብሐት ለወልድ 3X

ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ 3X

እውነትና ኃይልን በቸርነቱ የሚሰጠን ፣

ፍቅርና ጸጋን በየጊዜው ያካፈለን ፣

አምላክ ሲሆን አባት የሆነን ጌታ ፣

በጤናና በበረከት ኃይል ያቆየን ፣

ለገሩ ንጉሥ መድኃኒዓለም

ለጌትነቱ ፍጹም ምስጋና ይገባው

ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ኃያል ነው 3X

ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ኃያል ነው 3X

ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃያል ነው 3X

የአምልኮት ስግደት

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

ምስጋና አምልኮትና ውዳሴ ይገባው

ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

# የአምልኮት ስግደት

በአብ ስም አመልካለሁ 3X

በወልድ ስም እታመናለሁ 3X

በመንፈስ ቅዱስ ስም እባረካለሁ 3X

ለአብ እሰግዳለሁ 3X

ለወልድ እሰግዳለሁ 3X

ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ 3X

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ 3X

በማለዳ ንቁ

አብ አልፋና ኦሜጋ ነው 3X

ወልድ አልፋና ኦሜጋ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ አልፋና ኦሜጋ ነው 3X

አብ የባሕርይ አምላክ ነው 3X

ወልድ የባሕርይ አምላክ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ነው 3X

አብ ነድ ነው 3X

ወልድ ነድ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ነድ ነው 3X

ንቁ

አብ ፍሕም ነው 3X

ወልድ ፍሕም ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ፍሕም ነው 3X

አብ ነበልባል ነው 3X

ወልድ ነበልባል ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ ነበልባል ነው 3X

የተመሰገነ አብ ልዑል ነው 3X

የተመሰገነ ወልድ ልዑል ነው 3X

የተመሰገነ መንፈስ ቅዱስ ልዑል ነው 3X

የተመሰገነ አብ ታላቅ ነው 3X

የተመሰገነ ወልድ ታላቅ ነው 3X

የተመሰገነ መንፈስ ቅዱስ ታላቅ ነው 3X

የተመሰገነ አብ ክቡር ነው 3X

የተመሰገነ ወልድ ክቡር ነው 3X

የተመሰገነ መንፈስ ቅዱስ ክቡር ነው 3X

አብ መለኮታዊ ወርቅ ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ ወርቅ ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ወርቅ ነው 3X

አብ መለኮታዊ ጦር ነው 3X

ወልድ መለኮታዊ ጦር ነው 3X

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ጦር ነው 3X

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ይገባል 3X

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል 3X

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ መገዛት ይገባል 3X

ለጌታዬ ለሥላሴ ምስጋና ይገባል 3X

ለንጉሤ ለሥላሴ ምስጋና ይገባል 3X

ለአምላኬ ለሥላሴ ምስጋና ይገባል 3X

ለአለቃዬ ለሥላሴ ምስጋና ይገባል 3X

በረከቱን ላካፈለን ፣

ኃይሉን ላበዛልን ፣

በዚህ ሰዓት ላዳረሰን ፣

በዚህ ቦታ ላይ ላቀመን ፣

በቸርነቱ መንገድ ለመራን ፣

ሥጋወ ደሙን ለኛ ለሰጠን ፣

ክብር ምስጋና አምልኮት ይድረሰው

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

ለወላዲተ አምላክ ልጅ

መገዛት መስገድ ይገባል

ለዘላለሙ አሜን።

የአምልኮት ስግደት

# የጸሎት ቤት መርሃግብር

## ጸሎት ቤት ስዕለ አድኖ አቀማመጥ

- ❖ በመቆም ልክ ከግንባር ትይዩ የሥላሴ ፥ ከግራ የመድኃኒዓለም ፥ ከቀኝ የስቅለቱ
- ❖ በመንበርከክ ልክ ከግንባር ትይዩ የእመቤታችን ፥ ከግራ የቅዱስ ሚካኤል ፥ ከቀኝ የቅዱስ ገብርኤል
- ❖ ከበታች የሌሎች ቅዱሳንን ስዕለ አድኖ

## ሰባቱ የጸሎት ሰዓታት

ለሊት 11:00 ☞ ውዳሴ ማርያም፣ ሰይፈ መለኮት፣ ሰይፈ ሥላሴ የዘወትር

ጠዋት 3:00 ☞ መልክአ ገብርኤል፣ መዝሙረ ዳዊት፣ አርጋኖን

ቀትር 6:00 ☞ መልክአ ሚካኤል፣ መልክአ ሥላሴ

ቀን 9:00 ☞ መልክአ መድኃኒዓለም፣ መልክአ ዑራኤል

ከሰዓት 11:00 ☞ ውዳሴ ማርያም፣ ሰኔ ጎለጎለታ፣ የምሕላ ጸሎት፣ መልክአ ፋኑኤል

ማታ 3:00 ☞ አርጋኖን፣ መልክአ ሩፋኤል

እኩለ ለሊት 6:00 ☞ መልክአ ሥላሴ፣ መልክአ ሚካኤል፣ መዝሙረ ዳዊት

ለሊት 9:00 ☞ መልክአ ኢየሱስ፣ መልክአ ማርያም

## የጸሎትና የስግደት ቀደም ተከተል

1ኛ ✔ መጀመሪያ ጸሎት ቤታችሁ (ትንሽዬ ቤተመቅደሳችሁ) ከመግባታችሁ በፊት ፊታችሁንና እጅ እግራችሁን ታጥባችሁና ንጹሕ ሆናችሁ ተዘጋጁ። ደመ ጽጌ (ለሴቶች) በሚሆንበት ወቅት ከተቻለ ሙሉ ሰውነት ታጥባችሁ ቢሆን መልካም ነው።

ምክንያቱም፦ ለእግዚአብሔር ንጹሕ መሥዋዕት ይሰጣልና። የጸሎት ቦታን የማክበር መግለጫ ነው።

2ኛ ✔ ከተቻለ ነጭ አልባስ ብትለብሱ መልካም። ካልሆነ ግን ነጠላ አይጠፋም።

ምክንያቱም፦ ክርስቶስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ብሏልና ነጭ ብርሃንነቱን ወክለን በእኔ የሚመላለስ ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ያለውን የተስፋውንና የቃልኪዳኑን ቃል እንደዛለንና፤ ብርሃንነቱን በነጭ ነጠላ እንገልጻለን።

3ኛ ✔ እንደ ገባን በመቆሞ ልክ ከሥላሴ ስዕል ትይዩ እንሆንና ሦስት ጊዜ እናማትባለን። ካማተብንም በኋላ በቅዱሳን ስሞቹ ጸሎታችንና ስግደታችንን በመባረክ፤ በሰዓቱ እና በጊዜው ላደረሰን እና ላቆመን አምላክ ምስጋና ከማድረስ መጀመር።

4ኛ ✔ በመቀጠል መዝሙር 22'ን እንደ መግቢያ ጸሎት መጸለይ።

[ እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ። ]

5ኛ ✔ አስከትለን በዛው "አባታችን ሆይ" እንላለን

6ኛ ✔ ቀጥለን ከቆምንበት የሥላሴ ትይዩ ስዕል ሆነን ጸሎታችችንን እንዲባርክልና እንዲያጸድቅልን ጠይቀን የአምልኮት ስግደት መስገድ።

7ኛ ✔ ስንጨርስ ተንበርክከን የሰዓቱን_ጸሎት

ማለትም ለምሳሌ ምሽት 3፡00 ከሆነ ጸሎተ አርጋኖን፤ ሌሊት 11፡00 ከሆነ ውዳሴ ማርያም ማድረስ።

8ኛ ✔ በአባታችን ሆይ የሰዓቱን ጸሎት መዝጋት

9ኛ ✔ የግል ጸሎታችንን ማድረስ (ርዕስ ሰጥተን የምናደርሰው ወይንም የምንጠይቀው የግል ጸሎት)

10ኛ ✔ ጸሎቱን ካደረስንም በኋላ መቁጠሪያችንን አንስተን በመለኮተ ስሞቹ በመባረክ፤ በመቀጠል አሁንም በመለኮተ ስሞቹና የቅዱሳንን ስሞች እየጠሩ ጠላትን መቀጥቀጥ። የመሸገ ክፉ መናፍስትን ለመለየት ጀርባን፣ ሁለቱንም ትከሻዎች፣ ጭንቅላትንና ሆድን በእምነት ስሞች ተቃጠል እያሉ መቀጥቀጥ።

11ኛ ✔ በመቀጠል ሁለተኛ የአምልኮት ስግደት መስገድ። ያደፈጠውን መንፈስ ግንባር ላይ በሰማያዊ ስሞች አስረነው፤ ግንባራችንን የእንጨት መስቀል ላይ አሊያ ቅዱሳን ስዕላት ላይ ወይንም ጸሎተ መጽሐፍ ላይ እያስነካን ስንሰግድ፤ መንፈሱ በጣም ይቃጠላል። አስቀድሞ ከሰገድነው የአምልኮ ስግደት ይኸኛው የሚለየው ይሄ መንፈሱን ካዳከምን በኋላ፤ የጠላት መንገድ ለመዝጋትና ለማዳከም 'አብረኸኝ ስገድ 'ብለን ትእዛዝ ሰጥተን ስለምንሰግድ ነው።

13ኛ ✔ ጸሎታችንንና ስግደታችንንም ተቀበለን ብለን ከሁለተኛው ስግደት በኋላ መዝጊያ ጸሎት እንጸልይና በአባታችን ሆይ እንጨርሳለን።

☞ ተጨማሪ በዛው የንስሐና የቅዱሳን የሌሎችንም ጸሎታት የምናቀርብ ከሆነ ጸሎቱን ሳንዘጋ እንቀጥላለን።

ማስታወሻ፦ ይህ የጸሎት ቤት የመርሃ ግብር ቅደም ተከተል በሥርአት መልኩ የሚወሰድ አይደለም። የግል ተሞክሮን ከማካፈል አንፃር፣ መረጃ ከማቀበል አንፃርና መንፈሳዊነትን ከማሳደግ አንፃር የቀረበ መሆኑን ለማሳወቅ እወዳለሁ። ግዴታ ይህንን መንገድ መከተል አለባችሁ፤ ከዚህ የዘለላችሁት አሊያ ቅደም ተከተሉን ያልጠበቃችሁት ተሳስታችኋል የሚል ነገር የለም። ልባችሁ በፈቀደው ቅደም ተከተል ልክ መበርታት ነው። እግዚአብሔር የቢሮክራሲ አምላክ አይደለምና የአካሄዳችንን ጥራት አይቶ የሚቀበል አባት አይደለም። በጸሎትና በምስጋና ጊዜ ዋናው ከፍቅርና ከእውነት የተነሣ መሆኑ እንጂ በጸሎት አካሄዱ መሠረት አይደለም እግዚአብሔር የሚያስተናግደው።

## በስግደት የጸሎትን መንገድ መክፈት

### በስግደት የጠላትን መንገድ መዝጋት

ሰብአ ሰገል ሰማያዊ ኮከባቸውን የብርሃን ምሪት አድርገው ወደ ክርስቶስ መንገድ ድርሰው 'ወድቀው ከሰገዱ' በኋላ፤ ወደ አዋፊው ንጉሥ እንዳይመለሱ ሌላ የእግዚአብሔርን መንገድ አግኝተው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

እንዲሁ በአምልኮት ልምምድ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መንገድ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እየተመራን ስንጓዝ፤ የጸሎት ኃይላችን መለኮታዊ አቅም እንዲኖረው፣ የውስጥ እምነታችን እንዲጨምርና ሰማያዊ ጉልበታችን እንዲበረታ የዕለቱን የሰዓት ጸሎት ከመጀመራችን በፊት ቀድመን የቃል-ኪዳን ጸሎት አድርሰን መስገድ የጸሎታችን መንገድ ይከፈትልን ዘንድ መልካም ያደርግልናል። እንዲህ ስንል የቃል-ኪዳን ጸሎት ማድረስ እንችላለን።

"አባት የሆንከን እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፥ ጸሎተ ጊዜያችንን በመስቀል ብርሃንህ ቀድስልን። አቤቱ የቸርነትህ ፍቅር በባሕሪያችን፣ በጠባያችን፣ በአሳባችን፣ በእቅዳችን፣ በመሻታችን፣ በምግባራችን ውስጥ ተቀርጾ ይታተም ዘንድ እንለምንሃለን።

ቅዱስ አምላካችን ሆይ፥ የጸሎት ጊዜያችን መንገዱ ላይ ቀኝህን ትሰደድልን ዘንድ፤ መለኮታዊ ምሪትህ አስቀድሞ እያለፈ ይመራን ዘንድ፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተከተለ ያበረታን ዘንድ በስምህ ስለስምህ እንሰግዳለን"

## የጸሎት መንገድ መክፈቻ የአምልኮት ስግደት

ለአብ እሰግዳለሁ

ለወልድ እሰግዳለሁ

ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ

ምስጋና ይሁን ለአብ

ምስጋና ይሁን ለወልድ

ምስጋና ይሁን ለመንፈስ ቅዱስ

ሃሌሉያ ለአብ

ሃሌሉያ ለወልድ

ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ

በረከቱን ለሰጠን

ኃይሉን ላበዛልን

በዚህ ሰዓት ላቆመን

በቸርነቱ መንገድ ለመራን

በዚህ ሰዓት በጸጋው ለጠበቀን

በብርሃኑ መንገድ ለመራን

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

የድንግል ማርያም ልጅ

ክብር ምስጋና ይግባው

ለዘለዓለሙ አሜን።

በ
ማ
ለ
ዳ
ን
ቁ

ንቁ

እንደዚህ ሰግደን፤ እንደ ሰብአ ሰገል የጸሎት ጉዞአችንን ከመጀመራችን በፊት የነፍስ ኮከባችንን ካበራን በኋላ፤ የዕለቱን ምስጋና፣ የሰዓቱን የምንባብ ጸሎት፣ እና የግል የቃል ጸሎት ከጨረስን በኋላ ደግሞ፤ በመቁጠሪያ ጠላትን ቀጥቅጠን፤ መዝጊያ ስግደት እንሰግዳለን። ይሄ ስግደት ከመጀመሪያው የጸሎት መክፈቻ ስግደት የሚለየው፤ አንደኛ ያመሰገንነው ምስጋና ላይ፣ የምንባብ ጸሎት ላይ እና የግል መጠይቅ ጸሎታችን ላይ የማሰረገጫ ማኅተም መትቶ በአምልኮት ለማስጸደቅ ሲሆን፤ ሁለተኛው በጸሎት ያቃጠልነውን ጠላት የጥፋት መንገዱን ለመዝጋት፣ ከውስጣችን ተቀምጦ ጠቡን፣ አለመከናወኑን፣ እርግማኑን፣ ግራ ዘመሙን፣ ጤና፥ ሰላምና በረከት ማሳጣቱን እንዳይመራ የክፋት ግብር መንገዱን ለመዝጋት እንድንችል ነው። በመሆኑም "በሥላሴ ስም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ በድንግል ማርያም ስም፣ በቅዱስ ሚካኤል ስም፣ በቅዱስ ገብርኤል ስም ወዘተ.. በጸሎት የተቃጠልክ አጥፊ መንፈስ እስከ ሠራዊትህ ግንባር ላይ ታሰረህ፤ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱር ኃይለ ሥልጣን አብረህ ሰገድ" ብሎ በማዘዝ ግንባርን የጸለይንበት የጸሎት መጽሐፍን እያስነካን የጠላትን መንገድ ለመዝጋትና እንዲዳከም ደግሞ ሁለተኛውን የአምልኮት ስግደት እንሰግዳለን።

## የጠላት መንገድ መዝጊያ የአምልኮት ስግደት

እሰግድ ለአብ

እሰግድ ለወልድ

እሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ

እሰግድ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ 3X

ቅዱስ እግዚአብሔር ኃይል ሁነኝ

ቅዱስ ኃያል ሥልጣን ሁነኝ

ቅዱስ ሕያው ብርታት ሁነኝ

ቅዱስ አዶናይ ጉልበት ሆነኝ

ቅዱስ ኤልሻዳይ ግርማ ሁነኝ

ቅዱስ ያሕዌ ጽናት ሁነኝ

ቅዱስ ጸባዖት ምርኩዝ ሁነኝ

ቅዱስ ማሲያስ በረከት ሁነኝ

ቅዱስ ትስቡጣ ጸጋና ሞገስ ሁነኝ

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል አሜን።

ለሚያስደነግጥ መለኮታዊ መብረቅ እሰግዳለሁ

ለተንቦገቦገ መለኮታዊ ፍሕም እሰግዳለሁ

ለተወርዋሪ መለኮታዊ ቀስት እሰግዳለሁ

ንቁ

ለሚያቃጥል መለኮታዊ እሳት እሰግዳለሁ

ለሚያበራ መለኮታዊ ፋና እሰግዳለሁ

ለአንጸባራቂ መለኮታዊ ፀሐይ እሰግዳለሁ

ክቡድ ለሆነ ዕብነ መለኮት እሰግዳለሁ

ለሚያንቀጠቅጥ መለኮታዊ ግርማ እሰግዳለሁ

ለሚንቦገቦግ መለኮታዊ ነበልባል እሰግዳለሁ

ላማረ መለኮታዊ ጋሻ እሰግዳለሁ

ለሰኩረ ኃይል መለኮታዊ ጦር እሰግዳለሁ

ለሚያቃጥል መለኮታዊ ግለት እሰግዳለሁ

ለአሸናፊ መለኮታዊ እዘዝ እሰግዳለሁ

ለረቀቀ መለኮታዊ ሥልጣን እሰግዳለሁ

ለብርሃናዊ መለኮታዊ ጸዳል እሰግዳለሁ

ለተሳለ መለኮታዊ ሰይፍ እሰግዳለሁ

ለሚያስፈራ መለኮታዊ ቃል እሰግዳለሁ

በማለዳ ንቁ

ለአሰደናቂ መለኮታዊ ነበልባል እሰግዳለሁ

ለሚቆራርጥ መለኮታዊ ገጀሞ እሰግዳለሁ

ለንጹሕ መለኮታዊ ባሕርይ እሰግዳለሁ

ለጽኑ መለኮታዊ ምሣር እሰግዳለሁ

ለምጡቅ መለኮታዊ ተራራ እሰግዳለሁ

ለተነጣጠረ መለኮታዊ ቀስት እሰግዳለሁ

ለትኩስ መለኮታዊ ሙቀት እሰግዳለሁ

ነበልባሉን ላስረዘመ መለኮታዊ እሳት እሰግዳለሁ

ለአሸናፊ መለኮታዊ ኃይል እሰግዳለሁ

ገዥነት ላለው መለኮታዊ ገናንነት እሰግዳለሁ

የአድማስ ስፋት ላለው መለኮታዊ ብርሃን እሰግዳለሁ

በእሳት ለተከበበ መለኮታዊ ዙፋን እሰግዳለሁ

እውነት በእውነት ለዘላለሙ አሜን።

የጸሎታችን መነሻ መንገድ ላይ የአምልኮት ስግደት በመስገድ ብርሃን አብርተን፤ ጸሎቱን ስንጨርስ ደግሞ ሄሮድስ ያበራነውን መንገዳችንን አይቶ እንዳይከተል ኃይሉ ከድቶት ከኋላችን እንዲቀር በመቁጠሪያ ቀጥቅጠን አቅሙን ካወረድነው በኋላ እንዳይንቀሳቀስ በማሰር፤ የማጥፋት ጎዳናው እንዲዘጋና መዳከሙ እንዲጨምር፤ ሁለተኛውን ስግደት እንሰግዳለን።

**ማስታወሻ፦** ከላይ በተጠቀሱት ስግደቶች ፈንታ እንደ አቅማችን፣ እንደ ፍቅር መጠናችንና ጠላትን ለማድከም እንደመፈለግ መጠናችን ሌሎቹን ረዘም ረዘም ያሉትን የአምልኮት ስግደቶች መተካት እንችላለን። የሚተካ ሳይሆን በተጨማሪ የንስሐና የቅዱሳንን ስግደትን መጨመር መንፈሳዊ የነፍስ አቅምን ይጨምራል። ከላይ በተመለከተው የጸሎት መርሃ ግብር ላይ፤ ተራ ቁጥር ስድስትና እና ዐሥራ ሁለት ላይ ያሉ የመክፈቻና የመዝጊያ ስግደቶች ናቸው እነዚህ የጸሎት መክፈቻና የጠላት መንገድ መዝጊያ ተብለው የተጠቀሱት።

## አስጀምሮ ላስፈጸመን እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው።

*ከመምህር ግርማ ተማሪ ናትናኤል*